# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ በጥር 2018 ዓ.ም 8ኛ፣ 9ኛ፣ 10ኛ ና 11ኛ መደበኛ ስብሰባውን አካሂዷል፡፡ በአካሄዳቸው መደበኛ ስብሰባዎች የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2018 በጀት ዓመት የመንግሥትን የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም አስመልክቶ ከምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

ምክር ቤቱ በዚህ ወር የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ ያጸደቀ ሲሆን የፌዴራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞችንሹመትና የተለያዩሹመቶችንመርምሮአጽድቋል፡፡

የጥር ወር ዜና መጽሔታችን እነዚህንና ሌሎችን አበይት ምክር ቤታዊ ጉዳዮች ታስነብባለች፡፡

## ዓበይት ርዕሶች

- ህግ አወጣጥ
- ክትትል ቁጥጥር
- ሹመት

መልካም ንባብ!

ጥር፣ 2018ዓ.ም

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# ክትትል ቁጥጥር

የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ5ኛ ዓመት የሥራ ዘመኑ ጥር 26 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 10ኛ መደበኛ ስብሰባ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) የ2018 በጀት ዓመት የመንግሥትን የ6 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም አስመልክቶ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለቀረበላቸው ጥያቄዎቸና አስተያየቶች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡




## ክቡር የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለምክር ቤቱ ምላሽ ማብራሪያ ሲሰጡ

የምክር ቤት አባላት በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ፣ በሠላምና ደህንነት፣ በኑሮ ውድነት፣ በ7ኛው አገራዊ ምርጫ፣ በዲፕሎማሲ እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ጥያቄዎችና አስተያየቶችን አንስተዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማብራሪያቸው በግብርናው ዘርፍ የበጀት ዓመቱ ዕቅድ 7 ነጥብ 3 እድገት ለማስመዝገብ የታቀደ ሲሆን 1 ነጥብ 3 ቢሊየን ኩንታል ምርት እንደሚገኝ ታቅዶ በተለይ በክረምት ወራት ከፍተኛ ምርት የተገኘበት ዓመት በመሆኑ በ6 ወራት በተሰራው ስራ 999 ሚሊየን ኩንታል መሰብሰብ መቻሉን ገልጸዋል፡፡

ይህም ከበጀት ዓመቱ ዕቅድ አኳያ 78 በመቶ ይሸፍናል፡፡ በሰብል፣ በአትክልት እና ፍራፍሬ እንዲሁም በጥጥ ምርት የዓመቱን ዕቅድ 79 በመቶ በ6 ወራት መሸፈን መቻሉንም አንስተዋል፡፡ ባለፉት ስድስት ወራት ከወጪ ምርት የተገኘው 5 ነጥብ 1 ቢሊየን ዶላር ከዚህ ቀደም ባሉ ዓመታት ገቢ ተግኝቶ እንደማያውቅ ገልፀዋል፡፡ በተያዘው በጀት ዓመት ለውጪ ገበያ ከሚቀርቡ ምርቶች ለማግኘት የታቀደው 4 ነጥብ 2 ቢሊየን ዶላር ነበር ያሉት ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) ባለፉት ስድስት ወራት ብቻ 5 ነጥብ 1 ቢሊየን ዶላር ገቢ ማግኘት መቻሉንና የዕቅዱን 120 በመቶ አሳክተናል ብለዋል፡፡

አያይዘውም ከሀዋላ 4 ነጥብ 6 ቢሊየን ዶላር ገቢ የተገኘ እንደሆነና ይህም 39 በመቶ እድገት ማሳየቱን አውስተው የውጪ ቀጥተኛ 2 ነጥብ 3 ቢሊየን ዶላር አካባቢ የተገኘበት የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት 20 ነጥብ 6 በመቶ እድገት ማስመዝገቡን ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡

አያይዘውም ምርት ከውጪ ለማስገባት ወጪ ከተደረገው 11 ነጥብ 3 ቢሊየን ዶላር ውስጥ 39 በመቶው ምርት ለማምረት የሚያገለግሉ ግብዓቶችን ለመግዛት መዋሉን ጠቅሰው ከዚህ ቀደም ከውጭ ገቢ ይደረግ የነበረውን በሀገር ውስጥ ማምረት በመቻሉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን ማዳን ተችሏል ብለዋል፡፡

በለውጡ ጊዜ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዓመት በአማካኝ 8 ሚሊየን ሰዎች ያጓጉዝ የነበረ ሲሆን ባለፉት ስድስት ወራት 10 ነጥብ 7 ሚሊየን ሰዎችን ማጓጓዙን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በአገልግሎት ዘርፍ አመርቂ ውጤት ማስመዝገቡንም ገልጸዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ቢያንስ 22 ሚሊየን ለመድረስ እየተሰራ መሆኑንና ማሳካት ከተቻለ በለውጡ ወቅት ከነበረው አንጻር ከሁለት እጥፍ በላይ እንደሚያድግ እና አየር መንገዱ በቁጥር፣ በመዳረሻ፣ በትርፍና በሚያጓጉዘው ሰው እየጨመረ መሆኑን አብራርተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) በማብራሪያቸው በኢትዮጵያ የሞባይል ገንዘብ ዝውውር አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቁጥር 58 ሚሊየን መድረሱን ገልጸዋል፡፡

ከለውጡ በፊት የሞባይል ስልክ ተጠቃሚዎች ቁጥር 37 ሚሊየን እንደነበር አውስተው በአሁኑ ወቅት ኢትዮ ቴሌኮም ብቻ 87 ሚሊየን ደንበኞችን ማፍራቱን እንዲሁም ሳፋሪኮም ከ10 ሚሊየን በላይ ደንበኞች አሉት ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ከለውጡ ወዲህ የሞባይል ተጠቃሚው ቁጥር በ60 ሚሊየን መጨመሩን ገልጸው በአሁኑ ወቅት ከ97 ሚሊየን በላይ ሰዎች የሞባይል ተጠቃሚ መሆናቸውን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል።



ክቡር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበትን በተመለከተ ከምክር ቤት አባላት ለተነሳላቸው ጥያቄ ምላሽ ማብራሪያ ሲሰጡ የኑሮ ውድነት ችግር ምክንያቶች የምርት ፍላጎትና አቅርቦት መራራቅ፣ ከግብይት ስርዓቱ ጋር የተገናኘ እንዲሁም ዜጎች ያላቸውን ውስን ገቢ ለሚያስፈልጓቸውአስገዳጅጉዳዮችወጪለማድረግየሚመጣጠን ባለመሆኑ መሆናቸውን ገልጸው ምርትና ምርታማነትን ማሳደግና የዜጎችን ገቢ ማሳደግ ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በዚህም ምክንያት መንግሥት ባለፈው ዓመትና ዘንድሮ በተከታታይ ለሁለት ዓመታት የደመወዝ ጭማሪ ማድረጉን አስታውሰው ዋና መንግሥት ትኩረት እዳና ቀንበር ያልተጫነው ሀገርና ትውልድ መፍጠር ነው ብለዋል፡፡

አክለውም በየአካባቢዎቹ የተዘጋጁ የቅዳሜ እና እሁድ ገበያዎች ብዙ ችግር እየፈቱ ነው ብለዋል፡፡ ሰዎች የተለያዩ ምርቶችን በተሻለ ዋጋ በቀጥታ ከአርሶ አደሩ መሸመት የሚችሉባቸው ትልልቅ ገበያዎች እየተገነቡ መሆናቸውን እና ዘመን ገበያን የመሳሰሉ ዲጂታል የግብይት ስርዓቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ነው ብለዋል፡፡

መንግሥት በዋጋ ግሽበት የሚስተዋለውን ችግር ለመፍታት የበጀት አስተዳደርን ማስተካከል እንደሚገባ በመገንዘብ ከብሔራዊ ባንክ ብድር ሳይወስድ ዓመቱን ማሳለፍ የሚችልበትን ሁኔታ መፈጠሩን ጠቅሰዋል፡፡ እንዲሁም በርካታ ሥራዎችን በማከናወን በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የዋጋ ንረት ወደ ነጠላ አሀዝ መውረዱን ጠቅሰው ወደ 9 ነጥብ 7 በመቶ ዝቅ ማለቱን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል፡፡

ነዳጅ በተለያዩ ዓለም አቀፍና ቀጠናዊ ጉዳዮች ምክንያት ባለፈው ዓመት የነዳጅ ዋጋ መዋዠቅ ሲያሳይ እንደነበር የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት አንጻር ሲታይ በኢትዮጵያ የነዳጅ ዋጋ ዝቅተኛ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ክቡር ዐብይ አሕመድ (ዶ/ር) ከውጪ ተገዝቶና ወደብ ሳይኖረን በድጎማ ኃይል ከሌሎች ጎረቤት ሀገራት ባነሰ ዋጋ ነዳጅ እየቀረበ መሆኑን ጠቁመው በነዳጅ አቅርቦት ላይ የሚታዩ ችግሮች ዋነኛ መንስኤ ስግብግብ የሆኑ ሰዎች ከዚህ ድጎማ ለመቀራመት የሚያደርጉትን ጥረት በበቂ ሁኔታ መቆጣጠር አለመቻል ነው ብለዋል፡፡

በመሆኑም ዘመናዊ የክትትል ሥራ እየተሰራ እንደሆነና የእያንዳንዱን ነዳጅ ጫኝ ቦቴ እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር ብሎም ወደ ሀገር ውስጥ ከገባ በኋላ በእያንዳንዱ የነዳጅ ማደያ የቁጥጥር ሥራዎችን ለመሥራት እየተሞከረ መሆኑን ለምክር ቤቱ አብራርተዋል።

በድጎማ፣ ገቢን በማሳደግ፣ በግብይት ሰንሰለት፣ በመብራት እና ነዳጅ ዋጋ የተሰራው ሥራ የዋጋ ግሽበትን መቀነስ መቻሉን የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አህመድ (ዶ/ር) አሁንም የዋጋ ግሽበትን ለመቀነስ ዋና ዋና ጉዳዮች በሆኑት በምግብ፣ ቤት፣ ትራንስፖርት፣ ትምህርት ቤት ምገባ እና ገቢን በማሻሻል ረገድ በትኩረት እየተሰራ ይገኛል ሲሉ ለምክር ቤቱ አስገንዝበዋል፡፡

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አሕመድ (ዶ/ር) መንግሥት ባለፉት ዓመታት ካከናወናቸው ተግባራት መካከል የትምህርት ሥርዓቱን የማሻሻል ስራ መሆኑን ጠቅሰው በዚህም 34ሺ መዋዕለ ህጻናት ተገንብተው ከ4 ሚሊዮን በላይ ህጻናት መዋዕለ ህጻናት እንዲማሩ ዕድል ተፈጥሯል ሲሉ ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡

በሰው ሰራሽ አስተውሎት ዓለም እውቀት ነጻ እና በሁሉም ቤት እኩል ሊደርስ እንደሚችል ጠቅሰው ከታች ጀምሮ በመስራትና የዲጂታል ክህሎትን በመገንባት ለነገ ውድድር መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል፡፡ የዘንድሮው 7ኛው አገራዊ ምርጫ ሰላማዊ፣ ፍትሃዊና አካታች እንዲሁም ካለፈው ምርጫ የተሻለ እንዲሆን መንግሥት አበክሮ እየሰራ መሆኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐብይ አህመድ (ዶ/ር) ገልጸዋል፡፡
ምርጫውን በውጤት እንየው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህ ፓርላማ በብዙ መልኩ በርካታ ድምጾች የሚሰሙበና በምርጫ የሚሳተፉ ኃይሎችም ተጠቃሚ እንደሚሆኑ አብራርተዋል፡፡

ዲፕሎማሲ እና የቀጠናዊ ትስስር ጉዳዮችን አስመልክቶ ለተነሱ ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽና ማብራሪያ በጦርነት ሳይሆን በውይይት እና በዲፕሎማሲ ገበያ ኢትዮጵያ የቀይ ባህር ድርሻ እንዲኖራት ለማድረግ እየተሰራ ነው ብለዋል፡፡

የአፍሪካ ቀንድ እንዳይቀደድ የተሰፋ በትብብር እንዳይሰራ ደግሞ የብሔራዊ ጥቅም ችግሮች፣ ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት እና ፉክክሮች ያሉበት ቀጠና መሆኑን ገልጸው ቀጠናው በተፈጥሮ ሀብት የታደለ፣ የብዝሃ ቋንቋ እና ባህል ባለቤት መሆን ሲገባው አንዱ ለአንዱ ጋሻ ሲሆን ሌላኛው ጥይት አቀባይ በመሆኑ ተገቢውን ሰላም እና ዕድገት ማረጋገጥ እንዳልተቻለ አብራርተዋል፡፡

ውጥረቶችን ለማርገብ እና ቀጠናዊ ትስስርን ለማምጣት ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቅሰው ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ሊቀረፉ እንደሚችሉ ያላቸውን ተስፋ ገልጸዋል፡፡

ኢትዮጵያና ቀይ ባሕር ለዘለዓለም ተነጣጥለው መታየት አይችሉም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ በታሪክ የቀይ ባህር ባለቤት እንደነበረች አስታውሰው በጦርነት ሳይሆን በውይይት እና በዲፕሎማሲ ገበያ የቀይ ባህር ድርሻ እንዲኖራት ለማድረግ እየተሰራ ነው ሲሉ ለምክር ቤቱ አስገንዝበዋል፡፡

## ህግ አወጣጥ

**ምክር ቤቱ የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ አጸደቀ፣ 6ኛው የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በ5ኛ ዓመት የስራ ዘመኑ ጥር 14 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 9ኛ መደበኛ ስብሰባ የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን መርምሮ አጽድቋል፡፡**





የተከበሩ አፈ ጉባኤ አቶ ታገሠ ጫፎ ጉባኤውን ሲመሩ

ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሕዝባዊት ሪፐብሊክ ቻይና መንግሥት መካከል የተደረገውን የወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አስመልክቶ የህግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት መንግሥቱ ሪፖርትና ውሳኔ ሀሳቡን አቅርበዋል፡፡



የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት መንግሥቱ የውሳኔ ሃሳቡን ሲያቀርቡ

የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት በማብራያቸው ስምምነቱ እያደገ የመጣውን የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ ከፍታ ማሳያ መሆኑን ጠቁመው ሁለቱ ሀገራት በንግድ እና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያላቸዉ ግንኙነት እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ የሁለቱም ሀገራት ዜጎች በቀላሉ ወደ ሁለቱም ሀገራት መጓዝ በመቻላቸው ለወንጀል ክስ፣ ምርመራ እና ክስ ሂደት የሚያስፈልጉ መረጃዎች እና ማስረጃዎች እንዲሁም ለወንጀል መፈፀሚያነት የዋሉ፣ ሊዉሉ የታሰቡ ወይም የወንጀል ፍሬ የሆኑ ንብረቶች ሊሸሹ የሚችሉበት ዕድል ከፍተኛ በመሆኑ የተለያዩ የወንጀል መረጃዎችን ወይም ማስረጃዎችን በመለዋወጥ ተጠርጣሪዎችና ወንጀለኞች ከቅጣት የማያመልጡበትን ሁኔታ በመፍጠር የሕግ ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ይረዳ

ዘንድ ኢትዮጵያ ከቻይና ጋር በወንጀል ጉዳዮች የጋራ የሕግ ትብብር ማድረግ ሀገራችን እየተገበረች ላለችው የሕግ የበላይነት ማረጋገጥ ማሳያ ስለሆነ ስምምነቱ አስፈላጊ በመሆኑ ነው ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ምክር ቤቱም በስምምነት ረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ስምምነቱን አዋጅ ቁጥር 1402/2018 አደርጎ በአንድ

በተያያዘ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሕዝባዊት ሪፐብሊክ ቻይና መንግሥት መካከል የተደረገውን ፍርደኞችን የማስተላለፍ ስምምነት ረቂቅ አዋጅ አስመልክቶ የሕግ እና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ አቅርበዋል፡፡

ረቂቅ አዋጁ ኢትዮጵያ እና ቻይና ያላቸዉ ግንኙነት ለረጅም ጊዜ የነበረና በተለይም ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በንግድ እና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያላቸዉ ግንኙነት እየጨመረ የመጣ በመሆኑ በተለያዩ ወንጀሎች ምክንያት ዜጎቻቸው ተፈርዶባቸው ፍርዳቸውን በሀገራቸው ጨርሰው እና ታርመው ወደ ራሳቸው ማህበረሰብ መቀላቀል እንዲችሉ በማድረግ የመታረም ሂደቱን ውጤታማነት የሚያግዝ ነው ሲሉ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት አብራርተዋል፡፡

ስምምነቱ ፀድቆ ተግባራዊ መደረግ በሁለቱ ሀገራት መካከል የፍርደኞችን ማስተላለፍ ስነ-ስርዓት ሂደት ያገናዘበ፣ ዓለም አቀፍ አሰራርን መሰረት ያደረገና ውጤታማ የሆነ የፍርደኞችን ሰብአዊ መብት የጠበቀ ትብብር በማድረግ እና በሁለቱ ሀገሮች መካከል ዜጋ ተኮር የሆኑ ስምምነቶችን እና ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶችን ማጠናከር የሚችል የትብብር ማዕቀፍ ነው ሲሉ የስምምነቱን አስፈላጊነት አስገንዝበዋል፡፡

ምክር ቤቱም በስምምነት ረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሕዝባዊት ሪፐብሊክ ቻይና መንግሥት መካከል የተደረገውን ፍርደኞችን የማስተላለፍ ስምምነት ረቂቅ አዋጅን አዋጅ ቁጥር 1403/2018 አድርጎ በ 1 ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል፡፡

በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በብራዚል ፌዴራላዊ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገውን ፍርደኞችን የማስተላለፍ ስምምነት ረቂቅ አዋጅ መርምሮ አጽድቋል፡፡

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት መንግሥቱ በቋሚ ኮሚቴው የተዘጋጀውን ሪፖርትና ውሳኔ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

ስምምነቱ የፍርደኞችን ሰብዓዊ መብት ያከበረና ፍርደኞች በራሳቸው ሀገርና ማህበረሰብ ውስጥ የፍርድ ቅጣታቸውን ለማጠናቀቅ የሚያስችል ሥርዓት የሚፈጥር ነው ሲሉ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡

አክለውም የስምምነቱ አተገባበር በእንካ-ለእንካ መርህ መሰረት የሚፈጸም እንደሆነና የስምምነቱ ጸድቆ ተግባራዊ መደረግ በሁለቱ ሀገራት መካከል ፍርደኞችን የማስተላለፍ ሕጋዊ አግባብ የሚፈጥርና ፍርደኞችን የማስተላለፍ ሂደትን የሚያቀላጥፍ አሰራርን ይዘረጋል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ምክር ቤቱም በስምምነት ረቂቅ አዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ረቂቅ አዋጁን አዋጅ ቁጥር 1404/2018 አድርጎ በአንድ ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል፡፡

በተያያዘ ምክር ቤቱ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በደቡብ አፍሪካ ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገዉን በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን የአሳልፎ መስጠት ስምምነት ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አጽድቋል፡፡

የሕግና ፍትሕ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት መንግሥቱ ቋሚ ኮሚቴው ያዘጋጀውን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ አቅርበዋል፡፡

ኢትዮጵያ እና ደቡብ አፍሪካ ያላቸዉ ግንኙነት ለረጅም ጊዜ የነበረና በተለይም ደግሞ በአሁኑ ወቅት በንግድ እና ኢንቨስትመንት ዘርፍ ያላቸዉ ግንኙነት እየጨመረ የመጣ በመሆኑ ምክንያት ተጠርጣሪዎችና ወንጀለኞች ይህንን ሁኔታ በመጠቀም ከሕግ ለማምለጥ ወደ ሁለቱም ሀገራት ለመሄድ የሚችሉበትን አጋጣሚ ሰፊ ያደርገዋል ሲሉ የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት አስረድተዋል፡፡

የተከበሩ ወ/ሮ ዕፀገነት በማብራሪያቸው በወንጀል ጉዳይ ግለሰቦችን አሳልፎ መስጠትን አስመልክቶ የተደረገው ስምምነት ወንጀል የፈጸመ ግለሰብ ወይም ተጠርጣሪ ለፍትሕ ለማቅረብና ወንጀልን ፈጽሞ ወደሌላ ሀገር በመሸሸጉ ከተጠያቂነት እንዳያመልጥ ለማድረግ የሚረዳ ስምምነት ነው ብለዋል፡፡

የረቂቅ አዋጁ መጽደቅና ተግባራዊ መደረጉ በሁለቱ ሀገራት መከላከል የወንጀል ሥነ-ስርዓት ሂደት ያገናዘበ፤ ዓለም አቀፍ አሰራርን መሰረት ያደረገ ውጤታማ የሆነ የወንጀል መከላከል ትብብር ማድረግ የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና የፍትሕ ስርዓትን ለማስፈን ጠቀሜታው የጎላ ነው ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ረቂቅ አዋጁን አዋጅ ቁጥር 1405/2018 አድርጎ በአንድ ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ አጽድቆታል፡፡

በሌላ በኩል ምክር ቤቱ የተለያዩ ረቂቅ አዋጆችን ለዝርዝር ዕይታ ለቋሚ ኮሚቴዎች መርቷል፡፡

የሁሉንም ረቂቅ አዋጆች አስፈላጊነት አጭር መግለጫ በምክር ቤቱ የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ አቅርበዋል፡፡




የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ ማብራሪያ ሲያቀርቡ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በኮሪያ ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ መካከል ለህክምና መሳሪያዎች አቅርቦት ፕሮጀክት ምዕራፍ 2 ማስፈጸሚያ የተደረገውን የብድር ስምምነት ረቂቅ አዋጅ ፕሮጀክቱን ለማከናወን ከደቡብ ኮሪያው ኤክስፖርት-ኢምፖርት ባንክ የ30,000,000 የአሜሪካ ዶላር (ሰላሳ ሚሊዮን የአሜሪካ ዶላር) የተገኘው ቀላል ብድር የህክምና መሳሪያዎች ችግር የሚፈታና በጣም ዝቅተኛ ወለድ (0.01%)

የሚከፈልበት እንዲሁም በረጅም ጊዜ (አርባ ዓመት) የሚከፈል በመሆኑ ከሀገራችን የብድር ስትራቴጂ ጋር የሚጣጣም መሆኑን የተከበሩ ወ/ሮ መሠረት ኃይሌ ለምክር ቤቱ አስረድተዋል፡፡

የብድር ስምምነቱ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 5/2018 ሆኖ ለዝርዝር ዕይታ ለፕላን፣ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርቷል፡፡

የህብረት ሥራ ማሻሻያ ረቂቅ አዋጅን ለዝርዝር ዕይታ ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 6/2018 አድርጎ ለግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ የኢትዮጵያ አቪዬሽን ሴኩዩሪቲ ረቂቅ አዋጅን ረቂቅ አዋጅ ቁጥር7/2018 አድርጎ በዋናነት ለውጭ ግንኙነትና የሠላም ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በተባባሪነት ለከተማ ልማትና ትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም የፌደራል የስፖርት ልማት እና አስተዳደር ረቂቅ አዋጅን ረቂቅ አዋጅ ቁጥር 8/2018 አድርጎ ለጤና፣ ማሕበራዊ ልማት፣ ባሕልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ መርቷል፡፡





ም/ቤቱ የውሳኔ ሃሳቡን ሲያጸድቅ

## በተያያዘ ዜና ጥር 28 ቀን 2018 ዓ.ም በአካሄደው 11ኛመደበኛ ስብሰባ የተለያዩ ሹመቶችን አጽድቋል፡፡

ምክር ቤቱ በቅድሚያ የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የቦርድ አባላትን ሹመት አፅድቋል።

የሁሉንም ሹመቶች የውሳኔ ሃሳብ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ተጠሪ ሚኒስትር ዴኤታ የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ(ዶ/ር) አቅርበዋል፡፡

 

የተከበሩ ምህረቱ ሻንቆ (ዶ/ር) የውሳኔ ሃሳቡን ሲያቀርቡ

በዚህ መሰረት ምክር ቤቱ በቀረበው የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን የቦርድ ሰብሳቢ እና አባላት ሹመት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ከተወያየ በኋላ

1. የተከበሩ ዲያቆን ዳንኤል ክብረትን (ሰብሳቢ)
2. ክብርት ዶክተር መቅደስ ዳባን
3. ክቡር ዶ/ር እንደገና አበበ
4. ክቡር ዶ/ር አብዱልዋሳ አብዱላህን
5. ክቡር ዶ/ር ወርቁ ጋቻናን
6. ዶ/ር ጌታቸው ድንቁ
7. አቶ ቸሩ ጌታ ገነነን

8. አቶ ጃፋር በድሩን እና
9. አቶ የሱፍ ኢብራሂምን
በቦርድ አባልነት አድርጎ የውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 5/2018 በማድረግ በሁለት ተቃውሞ በአብላጫ ድምጽ ሾሟል።

ምክር ቤቱ በዚሁ ዕለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንቶችን እና የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞችን ሹመት ውሳኔ ሃሳብ ላይ ተወያቶ አጽድቋል፡፡

በዚህ መሠረት አቶ ልዑል ካህሳይን እና አቶ ምትኩ ማዳን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሹመት ውሳኔ ቁጥር 6/2018 አድርጎ በአንድ ድምፀ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።



የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንቶች ቃለ መሃላ ሲፈጽሙ

በተያያዘ ምክር ቤቱ በቀረቡለት 50 የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዕጩ ዳኞች ሹመት ላይ ከተወያየ በኋላ የቀረቡለትን ዕጩዎች ሹመት የውሳኔ ሀሳብ ቁጥር 7/2018 አድርጎ በአንድ ድምፅ ተዓቅቦ በአብላጫ ድምጽ አጽድቋል።

ተሿሚዎቹ በምክር ቤቱ ፊት ቀርበው ቃለ-መሀላ ፈጽመዋል።





## ለበለጠ መረጃና አስተያየት

### አድራሻ (Address)

ስልክ Tel:- 011-154-52-33
ነፃ ስልክ ጥሪ Free call 8557
ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box : 80001
ኢ.ሜይል E-mail info@hopr.gov.et

በኢ.ፌዴሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት የኮሙኒኬሽን፤ አስተህምሮና ሙዚየም መሪ ሥራ አስፈፃሚ የተዘጋጀ፤